# ደራሲው

ሐረግ፣ ቃላቶቹን ኣጥሜ፣ ኣጣጥሜ
ዓረፍተ-ነገሩን ገጥሜ፣ ኣጋጥሜ
ሞከርኹኝ በብዙ እንደቻለው ዓቅሜ
ተመጥጠ፣ ተመጥጠ ቀለሙም ደረቀ
ጻፍኩኝ፣ ለቀለቅኹኝ ብዕሬም ኣለቀ
ሓሳቤን ለመግለጽ ብጭር፣ ብጽፈው
ሰምቶ ያጤነውስ ከቶ ማን ሰው ነው?

የሚጮኽ ስላለ ያልሞላ ቆርቆሮ
ኣንዳንድ ዝምተኛ ራሱን ኣቀርቅሮ
ዝም በማለቱ ይመስላል ደንቆሮ
ምላሰ-ቀልጣፎች፣ በቃላትም ስልት
ሥልጣኔ ኣይገኝ በኣፍ ኣንደበት
ኣፍ የተናገረውን በእጁ ካልሠራ
ከንቱ ይባል የለ የሚጮኸ ደንቃራ

ሀ! ሁ! ብሎ ቆጥሮ ሞያን ሳያጠና
መቸም ኣይላቀቅ ከእንጀራ ልመና
ምላስ ቢቀለጥፍ ጠማማው ኣይቀና
ሰው መሳይ ሚዳቋ፣ ኣለሁ፣ ኣለሁ ባይ
ሲነግሩት ላይሰማ፣ ሲያሳዩት ላያይ
ሞያውን ሳይቀስም ኣዋቂ ተባለ
በጅራቷ ብይዛት ዓይኗ ፍጥጥ ኣለ

እነ ዓይነ ደረቅ ሁሌ ሲያፈጥጡብኝ
ኣዋቂ ለመምሰል ሲሞጣሞጡብኝ
በሆነ ባልሆነ ራስ ምታት ሆኑብኝ
ስሕተት በስሕተት ላይ፣ ከላዩ፣ ከላዩ
ማነው ኣታላዩ፣ ማነው ተታላዩ!
ሓሳብ በሥራ ላይ ማዋልን ካልቻሉ
ራሳቸውን እንጂ ማንን ኣታለሉ!

ቃሉን ኣድምጠውት ዚቁ ሳይገባቸው
የገባው ለመምሰል ሲሾል ምላሳቸው
እነሱም ተሞኙ፣ እኔም ታዘብኳቸው
ኣልገባንም ቢሉኝ እነግራቸው ነበር
ኣንግበውት ሄዱ ድንቁርናን ቀንበር

የገባው ለመምሰል ሁሉም ከደልለለኝ
ከእንግዴህስ በቃኝ፣ ውሸቱ መረረኝ

ገ/ኢ. ጐርፉ።